የሰ/መ/ቁ. 32217

ታህሣሥ 8 ቀን 2000 ዓ.ም.

ዳኞች፡- መንበረፀሐይ ታደሰ

ፍስሐ ወርቅነህ

ሐጎስ ወልዱ

ሒሩት መለሠ

ታፈሰ ይርጋ

አመልካች፡- ወ/ሮ እማዋይሽ አበራ

ተጠሪ፡- ወ/ሪት እልፍነሽ ሸዋዬ - ጠበቃ ዳኜ ረዳ ቀረበ፡፡

መዝገቡን መርምረን የሚከተለውን ፍርድ ሰጥተናል፡፡

## ፍ ር ድ

በዚህ መዝገብ ለቀረበው አቤቱታ መነሻ የሆነው ጉዳይ በውርስ ሃብት ክፍፍል ላይ ተመስርቶ የቀረበን ክርክር የሚመለከት ነው፡፡ ክርክሩ በተጀመረበት በትግራይ ብ/ክ/መ/በምስራቃዊ ዞን ከፍተኛ ፍ/ቤት ከሳሽ የነበረችው የአሁንዋ ተጠሪ ስትሆን፣ ከአባትዋ በውርስ አገኘሁ ያለችውን ንብረት እንዲያካፍሉዋት በአሁንዋ አመልካችና በሌሎች ሁለት ሰዎች /እህቶችዋ/ ላይ ክስ መስርታ ክርክሩ ተሰምቶአል፡፡ በመጨረሻም ተጠሪ ለክሱ ምክንያት ከሆነው ንብረት ላይ ድርሻዋን ትውሰድ ተብሎ ተወስኖአል፡፡ በሌላ በኩል ደግሞ አመልካች በተሰጠው ውሣኔ ላይ ባለመስማማት ለክልሉ ጠ/ፍ/ቤት ይግባኝ አቅርባ ክርክሩ በድጋሚ ከተሰማ በኂላ በከፍተኛው ፍ/ቤት የተሰጠው ውሣኔ ፀንቶአል፡፡ ውሣኔው መሠረታዊ የሕግ ስህተት አለበት ተብሎ እንዲሻር በሚል ለክልሉ ጠ/ፍ/ቤት ሰበር ችሎት የቀረበው አቤቱታም ተቀባይነት አላገኘም፡፡ አቤቱታው የቀረበው በዚሁ ላይ ነው፡፡

ይህ የሰበር ችሎት አመልካች ሐምሌ 12 ቀን 1999 ዓ.ም. በፃፈችው ማመልከቻ ያቀረበችውን አቤቱታ መሠረት በማድረግ ተጠሪን አስቀርቦ ክርክሩን ሰምቶአል፡፡ አቤቱታው በሰበር ችሎት እንዲታይ የተወሰነው አመልካች ይርጋን መሠረት በማድረግ ያቀረበችውን መቃወሚያ ውድቅ የመሆኑን አግባብነት ለመመርመር ነው፡፡ በዚህ መሠረትም ይህን ነጥብ በግራ ቀኝ ወገኖች ከቀረበው ክርክር፣ አቤቱታ ከቀረበበት ውሣኔ እና ከሕጉ ጋር አገናዝበን መርምረናል፡፡

ቀደም ሲል እንደተገለፀው ክርክሩ የውርስ ንብረት ክፍፍል የሚመለከት ሆኖ ተጠሪ ያቀረበችው የድርሻዬን ይሰጠኝ ክስ የይርጋ መቃወሚያ ቀርቦበታል፡፡ የስር ፍ/ቤቶች በሰጡአቸው ውሣኔዎች ላይ እንደተመለከተው የተጠሪ አባት ማለትም የንብረቱ የቀድሞ ባለሃብት የሞቱት በ1976 ዓ.ም. ሲሆን፣ ተጠሪ የውርስ ንብረት ይገባኛል ክስ የመሠረተችው ደግሞ በ1996 ዓ.ም. ነው፡፡ ፍ/ቤቶቹ በአመልካች በኩል የቀረበውን የይርጋ ክርክር ውድቅ ያደረጉት ከሣሽ ክሱን ያቀረበችው በፍ/ብ/ሕግ ቁ. 1000/2/ የተመለከተው የ15 ዓመት የጊዜ ገድብ ከማለፉ በፊት ነው የሚል ምክንያት በመስጠት እንደሆነም ተገንዝበናል፡፡

እንደምናየው የተጠሪ አውራሽ በሞቱበት እና ክሱ በቀረበበት ጊዜ መካከል ያሉት ዓመታት ሲቆጠሩ ከ20 ዓመት በላይ አልፎአል፡፡ ወራሽ የሆነው ሰው በሌላ ሰው የተያዘበትን የውርስ ሃብት ለማስመለስ ክስ መመስረት እንደሚችል በሕጉ የተመለከተ ቢሆንም፤ /የፍ/ብ/ሕግ ቁ. 999/ ክሱን የሚያቀርብበት ጊዜ ግን በሕግ ተወስኖአል፡፡ ከሣሹ መብቱንና የውርሱ ንብረቶች በተከሣሹ መያዛቸውን ካወቀ ሦስት ዓመት ካለፈ በኂላ ስለወራሽነት ጥያቄ የሚያቀርበው ክስ ተቀባይነት እንደሌለው በፍ/ብ/ብ/ሕግ ቁ. 1000/1/ ተመልክቶአል፡፡ በተያዘው ጉዳይ ተጠሪ ይመለስልኝ የምትለው የውርስ ሃብት አመልካች እንድትመልስላት ክስ የመሠረተችው በአመልካች መያዙን ካወቀች የሦስት ዓመት ጊዜ ከማለፉ በፊት ነው የሚል በፍሬ ነገር ረገድ የቀረበ ክርክር የለም፡፡ ይልቁንም ተጠሪ ክሱን የመሠረተችው የሦስት ዓመት ጊዜ ካለፈ በኂላ እንደሆነ ነው በሥር ፍ/ቤቶች ጭምር ግንዛቤ የተወሰደው፡፡ በዚህ ዓይነት ሁኔታ በሕጉ የተመለከተው የሦስት ዓመት የጊዜ ገደብ ካለፈ ደግሞ ወደ 15 ዓመት የሚኬድበት ምክንያት የለም፡፡ በፍ/ብ/ሕግ/ቁ. 1000/2/ የተመለከተው የ15 ዓመት የጊዜ ገደብ አስፈላጊ የሚሆነው በንኡስ ቁ. /1/ በተቀመጠው